# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org


በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ
በግንቦት 20 ቀን 2010 ዓ.ም. የተላለፈ ሐተታ

## ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት

እየገደሉ ይማርህ፤ እየቀበሩ እግዜር ያጥናህ፤ እያጠፉ ፖሊስ ይፈልግህ ፤ እያሰሩ ዕድሜ ይፍታኽ፤ እያባረሩ በሄድከበት ይቅናኽ ፤ እያስራቡ መልካም ዕራት የሚል ቋንቋ በመጠቅም የተካነው የወያኔ ቡድን፤ አሁን ደግሞ አዲስ የማታለያ ዘዴ ይዞ ቀርቧል። የሕዝቡን ጩኸት በመቀማት፤ የራሱ ብሶት አስመስሎ የሚጮኽለት አስመሳይ ቡድን አሰልፎ አሰማርቷል። ቡድኑም፤ የተሰጠውን አዲስ ተልዕኮ ሳያዛንፍ በመወጣት አኳያ አልተሳካለትም ማለት አይቻልም ። የወቅቱን የፖለቲካ ድራማ ፤ከሞላ ጎደልም ቢሆን፤ እየተወጣው ነው የሚሉ ታዛቢዎች ጥቂቶች አይደሉም።

እንዲያውም አልፈው -ተርፈው፤ ሁኔታውን ወዴት እንደሚያመራ እሰኪ እንየው የሚሉም አልታጡም። ለሃያ ሰባት ዓመታት የኢትዮጵያን ስም መጥራት ይቅርና መስማት እንኳ ሲያንገገፈግፈው የቆየው ቡድን ዛሬ ተነስቶ ኢትዮጵያ ! ኢትዮጵያ ! በማለቱ ብቻ የለውጥ ብርሃን መጥቷል ብለው የሚናገሩም አልታጡም። ይኽም " ያልወለድኩት ልጅ አባባ ቢለኝ ፤ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ " ከማለት የሚያልፍ ፋይዳ አያመጣም። በሕዝብ ትግል ምክንያት እየተለወጠ በመጣው ሁኔታ አስገዳጅነት ፤ወያኔዎች ፤አዛናኒ የሆኑ የገለሰቦች ብወዛ ስላደረጉ ብቻ፤ መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች ሊረግቡ አይችሉም።

ሕዝብ ለአነሳው ጥያቄ ጊዜ ስጡኝ ሊል የሚችል ጨቋኙ አገዛዝ እንጅ ፤ የሕዝብ ወገን የሆነ ክፍል አይደለም። አልፎ - አልፎ ግን ስለ ጊዜ ጉዳይ የሚያነሱ ክፍሎች እንዳሉ ባይዘነጋም፤ ጊዜ የሌላት ሀገር ፤ ከየት አምጥታ ጊዜ መስጠት እንደምትችል ግን መረዳትም ሆነ ማስረዳት ያስቸግራል። ያ መከረኛው የሦስት ሽህ ዐመት ጊዜ የሚጠቀስ ከሆነ ደግሞ ፤ ለታሪካችን ማጣቀሻ ከመሆን አልፎ-ተርፎ ፤ ኢትዮጵያ አሁን ለገጠማት የሞት -ሽረት ትግል ካለፈው ታሪኳ የምትበደረው በቂ ጊዜ ያላት ሀገር አይደለችም። ጊዜ ቢተርፋትም እንኳ ጊዜዋን ተጠቅማ ፤ ጊዜው አልፎበት ለመሞት የሚንገዳገደውን ዘረኛ ሥርዓት ከመገርሰስ በቀር ሌላ ምርጫም ሆነ ጊዜ አይኖራትም ።

ኢትዮጵያ ፤ ምናልባት ስቃይዋን ለማስታመም ጊዜ ይኖራት እንደሆን እንጅ፤ በሽታዋን ለማስወገድ በምታደርገው ትግል ለአንድ አፍታም ቢሆን ጊዜዋን እንድታባክን አይጠበቅባትም። በሽታን ማስወገድ ጊዜ የማይሰጠው ርምጃ እንደሆነ ሁሉ፤ ዘረኛውን ሥርዓት ለማስወገድ ማቅማማት አስፈላጊ አይደለም ። ከቶውንም፤ ሕዝባዊው ዐመፅ እተቀጣጠለ ዘረኛውን ሥር ዓት እያርበተበተ በመጣበት ሰዓት ፤ ትግሉን ወደፊት መቀጠል እንጅ፤ ለወያኔ ማንሰራሪያ የሚጠቅም ፋታ መስጠት፤ ጎጅ እንጅ ፋይዳ አያመጣም ። ኢትዮጵያ ሀገራችን በየጊዜው የሚመጣላትን መልካም ጊዜ ሳተጠቀምበት እየቆየች በተደጋጋሚ መቋጫ ወደማይገኝበት አዙሪት ገብታ ፍዳዋን ታያለች። ከዚኽ ዙሪያ ጥምጥም በግድ መውጣት አለባት።!

አዲስ ከስተት ሲከሰት፤ከግርታ የተነሳ ፤ እስኪ ቆየት ብለን እንየው ማለት ያባት በመሆኑ ፤ አያስነውርም። አንድ አንድ ክፍሎች ፤ ይኸንን አቋም ቢወስዱ የግል አስተሳሰባቸው በመሆኑ፤ መረዳት አያስቸግርም። አያስገርምም። ። በማነኛውም ፀረ ኢትዮጵያ ኃይል ትግል ላይ ተፃርሮ መቆም አከራሪነት ሳይሆን ፤ የመርኅ ጥንካሬን የሚያረጋግጥ፤ ዘመን -ተሻጋሪ ፤ ትውልድ- አስከባሪ ተምሰሌት እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል ። በጠንካራ መርኅ ላይ መቆም እንደሚያስከብር ፤ የሀገራችን ታሪክ ያስተምረናል ፡፡

ወቅታዊው የወየኔ ድራማ፤ መዕከላዊ ነጥብ፤የሕዝቡን ጩኸት በመቀማት የእራሱ ጮኸት አስመስሎ በማቅረብ ፤ እያወናበደ የሥልጣን ጊዜውን ለማረዘም መፍጨርጨር እንደሚሆን ደግሞ ማስተዋል ይገባል ። የዚኽ ዘረኛ ሥርዓት ዕቅድ ፤ ለጊዜውም ቢሆን ፤ የሕዝቡን ትግል ጋብ ሊያደርግልኝ ይችላል ብሎ ያሰበውን፤ በሥራ መተርጎም እንደሆነ ገምቷል ፡፡ ግምቱ ዋጋ- ቢስ ነው ብሎ መደምደም የሚቻል አይደለም።

የወያኔን መሰሪነት ፤ የፈጣሪውን ያኽል ከሚያውቁት ኢትዮጵያውያን መካከል፤ ኢሕ አፓ የመጀመሪያው ነው ቢባል ማጋነንንም መመጻደቅም አይደለም። በመሆኑም፤ ወያኔ የሆነውን አንዳሎሆነ ፤ ያልሆነውን ደግሞ እንደሆነ ለማስመስለ የሚጥርና እንደ ዕሥሥት ተለዋዋጭ የሆነ ባኅርይ ያለው ፍጡር በመሆኑ፤የሕዝቡን ዐመፅ፤ ለመግታት እንደ አስፈላጊነቱ፤ የሚያገጥመውን ተለዋዋጭ ሁኔታው ለማስተናገድ የሚጥር ትዝቢ ድርጅት ነው። ዐላማውን ለማሳካት፤ የማይጭረው ፍልፈል -ዐፈር፤ የማይቆፍረው መቃብር፤ የማይቀላውጥበት ድግስ፤ አልነበረውም። ይኸንን ለማድረግ፤ የሀራችን ቀደኛ ጠላቶች ከነበሩት ሁሉ ጋር ሳይቀር ደጅ ጥንቶ ትብብራቸውን አግኝቷል ።

1ኛ. ከሶማሊያው ስያድ በሬ ጋር ተበብሮ የጦር መሣሪያና ገንዘብ በመግኘት የኢትዮጵያን ስትራተጂያዊ ጥቅም አሳልፎ የሰጠ ለውጭ ኀይል የሰገደ ተንበርካኪና ከሃዲ ቡድን ለመሆኑ በማስረጃ የተደገፈ ሀቅ አለ ።

**2ኛ.** ከሊቢያው ሙኣመር ጋዳፊ ዘንድ ትንበርከኮ፤ እኛ የመኖች ነን ብሎ በመቅረብ በሚሊዮን የሚቀጠር ዶላር አግኝቶ ከሀገራችን ቀንደኛ ጠላት ጋር የተባበረ ክሃዲ ጉጅሌ መሆኑ በተግባር አስመስክሯል ።

**3ኛ.** ከሌሎች ዐረባውያን ሀገራት ተባብሮ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን አስላፎ የሰጠ ወራዳ ቡድን ነው ።በተንበርካኪነቱም ፤ የዐረቦቹን ሁለንተናዊ ትብብርና ርዳት አግኝቷል።

በሃያ ሰባት የአገዛዝ ዘመን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንነት ውስጡን አብጠርጥሬ አውቀዋለሁ ከሚል የተሳሳተ ድምዳሜ ሊደርስ የበቃውም ፤ የሰራው የሀገር ክህደት ወንጀል፤ ተሸፍኖ የቀረለት ስለመሰለው ነው። እስካሁንም ፤ ጎሣን ከጎሣ፤ ኃያማኖትን ከኃይማኖት፤ አንዱን ቡድን ከሌላኛው እያጋጨ በሥልጣን ለመቆየት በቅቷል ። አሁን ግን ጥረቱ ሁሉ፤ ወሃ ሽታ እየሆነበት ይገኛል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠቡ፤ ከዘረኛ አገዛዝ መስራቾቹ ከወያኔዎች ጋር እንጅ ፤ከግለሰቦች ተዋንያን ጋር አይደለም ። ከዐብይ አህመድም ጋር ቢሆን ፤ በግለሰብ ደረጃ፤ ማንም ዜጋ ጥላቻና ጥብ ላይኖረው ይችላል ። የሥርዓቱ ጠባቂ ፤ አራማጅና ተከላካይ በመሆኑ ግን ከሚያስከትለበት ጠተጠያቂነት አንፃር፤ " **ከኑግ ጋር የተገኘኽ ሰሊጥ፤ አብርኽ ተውቀጥ !** " ከሚለው ኃላፊነት ሊያመልጥ የሚችል አይሆንም።

ከታሪክ ተጠያቂነትና ከትውልድ ወቀሳ ነፃ ሊሆን የሚችለው ግን፤ የወያኔን ዘረኛ ሥር ዓት ቦርቡሮ ለመገርሰስ በሚደረገው እንቅስቃሴ ሁነኛ ሚን ከተጫወተ ብቻ ነው። ይኸንን ጥረት ማድረግ ሲጀምር፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ትብብር የሚያጣ አይሆንም ። ያን ጊዜ ይሆናል፤ ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ፤ አብርህ ተወቀጥ ከመባል የሚድነው ።

ወያኔዎቹ ወደዱትም ጠሉት፤ ኢትዮጵያዊነት ከምን ጊዜውም በበለጠ አብቦና ፈክቶ፤ ተስፋፍቶና ተጠናክሮ በመውጣት ላይ ነው ። ያሃያ ሰባት ዓመታት የዘረኝነት ተውሳክ እየከሰመ ሄዷል። ሕዝብ ከፍርሃት ቆፈን ተላቅቋል። እርስ በእርስ መጠራጠርንና አለመተማመንን፤ እየተሸረሸረ፤ ቦታውን ለኅብረትና ለመግባባት እየለቀቀ እንደሆነ ብዙ ማስረጃዎች አሉ። እያንዳንዱ ዜጋ ፤ለራሱ ሕልውና ሲል ብቻ ፤ የኢትዮጵያን መኖር ከምንጊዜው በበለጠ አጥብቆ እንደሚሻ ያለጥርጥር በተግባር እያስመሰከረ ነው። በመሆኑም፤ የኢትዮጵያ መኖርና የዜጎቿ አንድነትና ነፃነት ለድርድር የሚቀርብ አንዳልሆነ፤ ሁሉም ተፈጥጦሚል ማለት ከሚቻልበት ደረጃ ተደርሷል ። " **ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው !"** መባሉ፤ ዜጎች በህዋሳቸው፤ በደም -በአጥንታቸው፤ በኅሊናቸው-በመንፈሳቸው ወዘተረ.... ሀገራቸውን ተለዋውሰውባታል ማለት ይመስለናል ። በዚኽ ስሜት የተሰረፀ ዜግነት ደግሞ፤ ማነኛውንም ውጣ-ወረድ ሁሉ ተቋቁሞ ፤ የኢትዮጵያን ዘለዓለማዊነት አስከብሮ ለትውልድ -ትውልድ ያስረክባል ።

ወያኔዎቹ " እኛ ከሌለን ሀገሪቱ ትፈርሳለች " የሚሉት ከንቱ ማስፈራሪያ፤ " ኢትዮጵያን የሚያፈራርሱ እነርሱ የፈራርሳሉ እንጅ ሀገሪቱስ አትፍርስም " በሚል ሕዝባዊ መልስ ተተክቷል ። ነባቢቱ በተግባር እየተለወጥ በመረጋገጥ ላይ ነው። አሁን በየቦታው የንፁህኑ የኢትዮጵያውያን ንፁኅ ደም በግፍ ይፈስሳል ። ወያኔ የመሰረተው ኮማድ ፖስት፤ ያለአንዳች ተቆጣጣሪ ኃይል በሠላማዊ ዜጎች ላይ ጦርነት አውጆ ጭፍጨፋውን አላቆመም ። ለውጭ ታዛቢዎች ፍጆታ ሲባል አስርና ሃይ እስረኞች እየፈታ፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ በመቶና በሽህ የሚቆጠሩ ዜጎች ውህኒ ይተጎራሉ። እስር ቤቶች አሁንም በንፁሃን ዜጎች ተጨናንቀዋል ። ስደት- ዘጽዓት አሁንም የዜጎቻችን ዕጣ ፋንታ እንደሆነ ቀጥሏል ። በወያኔ ዕስር ቤት የሚሰቃዩትን የኢትዮጵያ በርቅየ ታጋዮች፤ የኢሕአፓ አባላት አሁንም መዳረሻቸው የት እንደ ሆነ እንኳን ሊታውቀ አልተቻለም። የህዝብ መሠረታዊ ጥያቄ እስካልተመለሰ ድረስ ፤ ጥቃቅን ጥያቄዎች ምላሽ ሊያገኙ ይችላሉ የሚል ብዥታ ባይኖርም፤ የሥርዓት ለውጥ ወደ ሚያመጣ አቅጣጫ ሰጭ ምልክት እንኳን አይታይም። ያ አቅጣጫ ባለተከሰተበት ሁኔታ፤ የሕዝብ ምርጫ አሁንም ትግሉን አጠናክሮ ከመቀጠል በቀር ሌላ መፍተሄ የለም። የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ፤ ሕዝባዊ መሠረታዊ- ስትራተጃዊና የመርኅ ጥያቄ ነው። የሚሸራረፍ፤ የሚበወዝና የሚውሸለሸል መልስ አይጠብቅም። ተቀባይነትም አይኖረውም። በመሆኑ፤ ሕዝባዊው ትግል ይቀጥላል እንጅ አይገታም።

ዐብይ አህመድን በሃይለማርያም ደሳለኝ እንዲተካ ምክንያት የሆነው የሕዝብ ትግል እንጅ፤ የወያኔዎቹ የፖለቲካ ክኽሎት አንዳልሆነ ማንም የሚያውቀው ሀቅ ሆኗል ። ግለሰቦቹን ማሽጋሽግ ያሰፈለገውም ፤ በየዕለቱ እያገመገመ የመጣው ሕዝባዊ ዐመፅ ፤ ያስከተለውን መደናገጥ ለመረጋጋትና ከተቻለም አቅጣጫ ለማስለወጥም ጭምር ነበር ። ይኽ ዘዴ፤ የታሰበውን አሟልቷል ባይባልም፤ በጥቂቱም ቢሆን፤ ሕዝቡ በዐብይ አሕመድ የድራማ ተውኔት ላይ እንዲያተኩር አድርጎታል ቢባል ማጋነን ነው ማለት አይቻልም። የዐብይ መተካት፤ ለወያኔ መቆየት፤ የነፍስ አድን መርፌ ስለሆነለት፤ ለጊዜውም ቢሆን እፎይታን ሳይሰጠው አንዳልቀረ ይገመታል ። ያም ሆኖ ግን ፤ አሁንም የሕዝብ የሥር ዓት ለውጥ ጥያቄ አንኳር የትግል አሰባሳቢ ኃይል ሆኖ ቀጥሏል። ሕዝባዊው ዐመፅ ለጊዜው ጋብብ ብሎልኛል ብሎ ወያኔ ሊያስብ

ይችል ይሆናል ግን ይኽ የእነርሱ ብኽርታ እንጅ የሕዝቡን ቆርጠኝነት አይገልፅም ። ሕዝባዊው ዐመፅ ምሉዕ ሆኖ ቀጥሏል ። በአራቱም ማዕዘናት አንዱ ወገን ከሌላው ወገኑ ጋር እየተናበበ፤ ሁሉም በየፈርጁ እያተባበረ፤ ፀረ-ወያኔ ትግሉን አፍፍሞታል። ከእንግዲህ ወዲህ ቅንጣት ያኽል እንኳ ዕውነትነት በሌለው ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን እስከ መጨረሻው እያተላሉ መቀጠል አይቻልም ። በዚህ ኣይነት ቅጥፈት የተካኑት የናዚ ጀርመን ሊቀ-ካህህናት፤ እነ ጆሴፍ ጎብልስ ባቀጠጠሉት ዕሳት እራሳቸው ተቃጥለው የዶግ- አመድ ሆነው ቀርተዋል። ወያኔና ተከታዮቹ ከሕዝባዊ ዐመፅ ሊተርፉ የሚችሉት በአንገድ መንገድ ብቻ ነው። የሥር ዓት ለውጥ ሊወስድ ወደሚያስችለው የሠላማዊ ሽግግር መዘጋጀትና ሁሉንም የሚያሳትፍ ሀገራዊ ጉባዔ መጥራት ብቻ ! ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ሊጥልፏት ይሞክሩ ይሆናል፤ የ ኢትዮጵያን ሕዝብ ግን ማታለል አይችሉም !

ኢትዮጵያ ለ ዘለዓለም ትኖራለች !